# ም□ራአ 12

## □ብረ□ብና የሃይማኖት መቻቻል

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ አራት ዋና ዋና የትምህርት ርዕሶችን ትማራላችሁ። እነርሱም ሥነምግባር ግብረገብነትና ሃይማኖት፤ የሃይማኖት ብዝሃነት ሰብዓዊነትና ዴሞክራሲ፤ የሃይማኖት መቻቻል ሰላምና ልማትና የሃይማኖት ብዝሃነትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ልምድ የሚሉ ናቸው።

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ፡-**

- የየራሳቸውን የግብረገብ ልምዶች በመመርመር ከቤተሰባቸውና ከትምህርት ቤት የግብረገብ እሴቶች ጋር ያጣጥማሉ፤
- በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት ሕብረተሰብ ውስጥ የዴሞክራሲ ግንባታን ጥቅም ይረዳሉ፤
- የሃይማኖት መቻቻል ለአንድ ሀገር አንድነትና ልማት የሚኖረውን አስተዋጽኦ ያደንቃሉ።

### 12.1 ሥነ ምግባር ግብረገብነትና ሃይማኖት

### 12.1.1 ግብረገብ በግል ሕይወት ውስጥ

- ያላችሁን የግል የግብረገብ እሴቶች ልምድ ጥቀሱ።

ማንም ሰው በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙት እውቀትና ክህሎቶች ሁሉ ባለቤት ሊሆን አይችልም። ስለዚህም የሰው ልጆች የተለያዩ እሴቶችን፤ ልምዶችንና እውቀቶችን ይካፈላሉ። ይህም ሲባል ለየብቻቸው መኖር አይችሉም ማለት ነው። ምክንያቱም በማህበራዊ ተፈጥሮአቸው ምክንያት የአንዳቸው መኖር ከሌሎቹ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ነው።

አንድ ሰው ስለራሱ መኖር ሲያስብ ከሌሎች ጋር እንደሚኖርም ማሰብ አለበት። ከሌሎች ሰዎች ትብብርን፤ አክብሮትንና ሌሎች መልካም ባህሪያትን ይጠብቃል። የሚፈልገውን አክብሮትና ትብብር ለማግኘት ግለሰቦች ግብረገባዊ የሆኑ እሴቶችን መሰረት በማድረግ መንቀሳቀስ አለባቸው። በሕብረተሰቡ ውስጥም በጋራ የግብረገብ እሴቶች ላይ የተመሰረቱ ድርጊቶችን ማከናወን አብሮ በሰላም ለመኖር እጅግ ጠቃሚ ናቸው። ከዚያም አልፎ የሀገርን ኢኮኖሚ በቀጣይነት ለመገንባትም ይጠቅማል። ስለዚህ በግል ሕይወት ውስጥ ግብረገባዊ እሴቶችን

በመገንባት የሚፈለገውን ባህሪ በመቅረጽ ዜጎች ዘላቂነት ባለው ልማት ውስጥ እንዲሳተፉ ማስቻል ዋና ጠቃሚ ጉዳይ ነው።

- በሰብዓዊ ሕይወት ውስጥ □በዝሃነት መገለጫዎች፣ የልዩነትና የትብብር ማሳያዎች ምንድን ናቸው?

በሰብዓዊ ሕይወት ውስጥ ሰብዓዊ እሴቶች፣ ልምዶችና ተሞክሮዎች የተለያዩ ናቸው። ለልዩነቶቹ ምክንያቶች ሆነው ሊቀርቡ ከሚችሉ ውስጥ ባሕላዊ ዳራ፣ ሃይማኖት ወይም የትምህርት ደረጃን መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ፦ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮችና ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝቦች አባላት ልምዶቻቸውን፣ ክህሎቶቻቸውን እንዲሁም እውቀታቸውን አንድ ላይ ለልማት ሲያውሉት ሀገሪቷ ተጠቃሚ ትሆናለች። ይህም የሚገለጸው በመተባባር፣ በመቻቻልና በመከባበር ነው። ሕብረተሰቡ እንዲኖርና እንዲቀጥል እንዲሁም በጋራ ለመኖርና ለማደግ የግለሰቦች መኖር የግድ ያስፈልጋል። የግለሰቦች ችሎታ፣ ክህሎትና እውቀት የተለያዩ እንደመሆናቸው ለሕብረተሰቡ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦም የተለያየ ነው። ግለሰቦች ፍላጎቶቻቸውን ለማርካት የሚያስፈልጓቸውን አገልግሎቶችና ቁሳቁሶች የሚያገኙት ከሌሎች ግለሰቦች ነው።

ግለሰቦች ከሕብረተሰቡ ጋር የሚጋሯቸው የግብረገብ እሴቶች ለሰብዓዊ መብት መከበር መሰረት ናቸው። የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት፣ የተለያዩ የኢትዮጵያ ሕጎች፣ እንዲሁም የሰብዓዊ መብት ሕግ የጸደቁት ለሰው ልጆች በሰላምና በመከባበር መኖር ዋስትና ለመስጠት ነው። የሰው ልጆች የመኖር ጥቅም የሚገለጸው አንድ ሰው ለሌላው በሚሰጠው ክብር፣ በሰላም አብሮ መኖርና በማህበረሰቡም ሆነ በሀገሪቱ የልማት ስራዎች ላይ ለመሳተፍ በሚኖረው ቁርጠኝነት ነው።

**መልመጃ 1**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩባቸው።**

1. የእያንዳንዳችሁን የግብረገብ እሴቶች በመመርመር ሰብዓዊ ክብርን በመጠበቅ እና የጓደኞቻችሁንና የጎረቤቶቻችሁን የሃይማኖት መብቶች ከማክበር አንጻር ያላቸውን ድርሻ ግለጹ።
2. የሚጎድሏችሁን የስነምግባር እሴቶች ለዩ። በመቀጠልም እነዚህን ከመገንባት አኳያ ምን ማከናወን እንደሚጠበቅባችሁ ግለጹ።

### 12.1.2 ግብረገብ በቤተሰብና በትምህርት ቤት ውስጥ

- በአካባቢያችሁ ህብረተሰብና በትምህርት ቤታችሁ የሚገለፁ  የግብረገብ እሴቶች ምን ምን ናቸው?

ሕፃናት የግብረገብ እሴቶችን የሚማሩበት የመጀመሪያው  ተቋም  ቤተሰብ ነው፡፡ ከዚያም በመቀጠል ማህበረሰቡና ትምህርት ቤቶች የግብረገብ እሴቶቻቸውን ያጋሯቸዋል፡፡ በቤተሰቡ ውስጥ ወላጆችና በእድሜ ትልቅ የሆኑ አባላት ያሏቸው ልምዶች በልጆች ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ እነዚህ ልምዶች ግብረገባዊ እሴቶችን ወይም ግብረገብነት የጎደላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በማህበረሰቡ ተቀባይነት  ባላቸው የግብረገብ እሴቶች የሚመሩ ወላጆች መልካም ልምምዶችን ለልጆቻቸው ያካፍላሉ፡፡ በሌላ በኩል ማህበራዊ የግብረገብነት ጥሰት ያለባቸው ወላጆች እነዚህን ችግሮች ወደ ልጆቻቸው ያስተላልፋሉ፡፡

ትምህርት ቤቶች በሁሉም ተማሪዎችና በሌሎች የትምህርት ቤቱ አባላት ሊተገበሩ የሚገባቸው ሕጎችና ደንቦች አሏቸው፡፡ እነዚህ ሕጎችና ደንቦች በጋራ ተቀባይነት ባላቸው የግብረገብ እሴቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ በቤት ውስጥ ያሏቸውን ግብረገባዊ ልምዶች ይተገብራሉ፡፡ በተፃራሪው አንዳንድ ተማሪዎች በቤተሰባቸው ውስጥ የለመዱአቸው ግብረገባዊ ጥሰቶች ላይ የተመሰረቱትን ልምዶቻቸውን ይዘው ወደ ትምህርት ቤት ይመጣሉ፡፡

### *ሆንጋ*

*ሆንጋ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ ለቤተሰቡም የመጀመሪያ ልጅ ነው፡፡ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ሲማር ሆንጋ በጣም ጎበዝ ተማሪ ነበር፡፡ ቤተሰቡም የጽሕፈት መሣሪያዎች ሱቅ ነበራቸው፡፡ እናቱም ሆኑ አባቱ በንግድ ስራ ስለሚጠመዱ የልጆቻቸውን የትምህርት ሁኔታ ለመከታተል ጊዜ አልነበራቸውም፡፡*

*ቤተሰቡ ሆንጋ የሚጠይቀውን ገንዘብ ይሰጡታል፡፡ ሆንጋ ከትምህርት ቤት ብዙ ጊዜ ይቀራል፡፡ ለማርፈዱና ለመቅረቱ የሀሰት ምክንያቶችን ያቀርባል፡፡ ብዙውን ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ የማይወዱ ጓደኞች አሉት፡፡ በትምህርት ሰዓት ከትምህርት ቤት በመቅረት ቁማር ይጫወታሉ፡፡እነዚህ ተማሪዎች ተጨማሪ ገንዘብ ሲያስፈልጋቸው ይሰርቃሉ፡፡የቤት ስራዎቻቸውንም አይሰሩም፡፡ ሆንጋ ከርሱ ጋር የማይተባበሩ የክፍሉን ተማሪዎች ይሳደባል፡፡*

ሆንጋና ጓደኞቹ በፈተና ወቅት ይኮርጃሉ። የክፍል ኃላፊው መምህር ሆንጋና ጓደኞቹ ስለሚያደርጓቸው የግብረገብነት ጥሰቶች መረጃ ደርሷቸዋል።

ሆንጋና ጓደኞቹ ወላጆቻቸውን እንዲያመጡ በክፍል ኃላፊ መምህር ተጠየቁ። ከሁለት ቀናት በኋላ ሆንጋ አባቱ ያልሆኑ ሌላ ሰው ወደ ትምህርት ቤት አመጣ። የክፍል ኃላፊውም ሰውየው የሆንጋ አባት መሆናቸውን ለማረጋገጥ መታወቂያቸውን እንዲያሳዩው ጠየቃቸው። ሰውየውም መታወቂያ የለኝም አሉ። ሰውየው የሆንጋ አባት መሆናቸውን ሲጠይቅ አዎን ነኝ በማለት መለሱ። የክፍል ኃላፊው ሰውየውን የሆንጋ አባትና አያት ስሞችን እንዲነግሩት ሲጠይቃቸው መናገር አልቻሉም። ሆንጋም የግብረገብ ጥሰቶችን በመፈጸሙ ወላጆቹን እስኪያመጣ ድረስ ከትምህርት ቤት ታገደ።

**መልመጃ 2**

**ከላይ የቀረበውን አስረጂ መሰረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ።**

1. ከላይ ከቀረበው አሰረጂ ውስጥ የተገነዘባችሁትን የግብረገብ ጥሰቶች ዘርዝሩ።
2. የግብረገብ ጥሰቶችን ከሃይማኖቶች እሴቶች አንፃር ገምግሙና በተወካዮቻችሁ አማካይነት ለክፍሉ አቅርቡ።

ትምህርት ቤቶችም ሆኑ የሃይማኖት ተቋማት ወጣቱን ትውልድ በመልካም ስነምግባር የሚቀርፁ እሴቶች አሏቸው። ሁሉም ሃይማኖቶች የግብረገብ እሴቶችን ለተከታዮቻቸው ያስተምራሉ። ለትምህርት ቤቶች፣ ለሃይማኖት ተቋማትና ለቤተሰቦች የጋራ የሆኑ የግብረገብ እሴቶችን መተግበር ከህብረተሰቡ ይጠበቃል። ተማሪዎችም የህበረተሰቡ አካል እንደመሆናቸው የጋራ እሴቶችን መተግበር ይገባቸዋል።

**12.1.3 ግብረገብነት በማሕበራዊ ሕይወት ውስጥ**

- የወጣት ጥፋተኝነት ችግር ማለት ምን ማለት ነው?

ወጣት የሚለው ቃል እድሜያቸው ከ14 ዓመት አስከ 24 ዓመት ያሉትን የሚያጠቃልል ነው። በዚህ እድሜ ክልል ያሉ ሰዎች ግብረገብነት የጎደላቸውን ተግባራት ሲያከናውኑ የወጣት ጥፋተኝነት ችግር ይባላል።ለምሳሌ በቡድን መደባደብ፣ በግልና በጋራ ማመጽ፣ የትምህርት ቤትን ህጎች አለማክበር፣(በአጠር ሾልኮ መውጣት፣የሌላውን ንብረት መቀማት ወይም መስረቅ፣

ማርፈድ፤ ከትምህርት ቤት መቅረት፤ በትምህርት ሰዓት አልባሌ ቦታ መገኘት፤ ወዘተ) ሰዎችን መሳደብ፤ ከወጣት ችግሮች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው።

**መልመጃ 3**

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ።**

1. በሰፈራችሁና በትምህርት ቤታችሁ የታዘባችሁትን የወጣት ችግሮች ዘርዝሩ።
2. የወጣት አጥፊነትን ችግር በትምህርት ቤትና በአካባቢያችን እንዴት መፍታት እንደሚቻል ግለፁ።

### 12.1.4 የግብረገብ እሴቶች ጥሰት ችግሮችና መፍትሄአቸው

የወጣት ጥፋተኝነት ችግሮች የሚመጡት በጓደኛ ተጽእኖ፤ በቤተሰብ የአስተዳደግ ጉድለት ወይም በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ሊሆን ይችላል። በእንዲህ ዓይነት ተጽእኖዎች ሕፃናትና ወጣቶች ግብረገብነት ወደ ጎደሏቸው ድርጊቶች እንዲገቡ ያደርጓቸዋል። ግብረገብነት የጎደሏቸው ድርጊቶች በሰፈር፤ በትምህር ቤትና በአጠቃላይም በማህበረሰቡ ውስጥ ማህበራዊ ችግሮችን ይፈጥራሉ። ወጣት አጥፊዎች በገበያዎች፤ በታክሲና በአውቶቡስ ማቆሚያዎች እንዲሁም ሰዎች በሚሰበሰቡባቸው ቦታዎችና በየትምህርት ቤቶች አካባቢ በመንቀሳቀስ ግብረገብነት የጎደላቸውን ማህበራዊ ችግር በሚያመጡ ድርጊቶች ይሰማራሉ። ይህን ማህበራዊ ችግር ለመፍታት ቤተሰብ፤ ትምህርት ቤትና የሃይማኖት ተቋማት ቁልፍ ሚና መጫወት ይገባቸዋል።

ግብረገብነትን የተላበሱ ወጣቶች በልማትና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዋነኛ ተዋናይ ናቸው። በአንፃሩ ደግሞ የግብረገብ እሴቶች ጥሰት ችግር ያለባቸው ወጣቶች በቤተሰብ፤ በትምህርት ቤትና በህብረተሰብ ላይ ችግር ፈጣሪ ይሆናሉ። የግብረገብነት ችግሮች ያሉባቸው ወጣቶች በፍላጎታቸው ቡድን በመመስረት የተለያዩ የግብረገብነት ጥሰቶችን ልምድ ሲጋሩ ኃላፊነት ወደ ጎደለውና ማህበራዊ ችግሮችን ወደሚያባብሱ ድርጊቶች ይገባሉ። እነዚህም የግብረገብነት ጥሰት ድርጊቶች የህብረተሰቡን ሰላማዊ ሕይወት አደጋ ላይ ይጥላሉ። አነዚህን ችግሮች ለመፍታት የተለያዩ መንገዶች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ ቤተሰብና የሃይማኖት ተቋማት ወጣቶች መልካም ስነምግባር እንዲኖራቸው ለማድረግ ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና አለ። በትምህርት ቤቶችም የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ክበቦች፤የወላጆችና መምህራን ህብረትና የማህበረሰብ ፖሊስ ማዕከላት የየበኩላቸውን ሚና መጫወት ይችላሉ።

መልመጃ 4

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ።

1. በግለሰብ እና በማህበረሰቡ ደረጃ በሚከሰቱ የግብረገብነት ጥሰቶች መካከል ያሉት ልዩነቶች ምንድን ናቸው?
2. በግለሰብ ደረጃ የሚደረጉ የግብረገብ እሴቶች ጥሰቶች ወደ ማህበረሰብ የሞራል ጥሰቶች የሚያድጉት እንዴት ነው?
3. በግብረገብነት ጥሰቶች የሚከሰቱ ማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ መፍትሔዎቹ ምንድን ናቸው?

## 12.2 የሃይማኖት ብዝሃነት፣ ሰብዓዊነትና ዴሞክራሲ

### 12.2.1 የተለያዩ ሃይማኖቶች ባሉበት አገር ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብን መገንባት

- ዴሞክራሲ በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት ህብረተሰብ ውስጥ መገንባት ጥቅሙ ምንድን ነው?
- ዴሞክራሲ በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት ህብረተሰብ ውስጥ ባይገነባ ምን ችግር የሚፈጠር ይመስላችኋል?

በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት አገር ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን መገንባትና መተግበር በጣም ጠቃሚ ነው። ይህም የብዝሐ-ሃይማኖት መብቶችን ጨምሮ ሌሎች መብቶችም በእኩልነት እንዲከበሩ ስለሚያደርግ ነው።የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ሰነዶች ሰብዓዊ መብቶችንና ሰብዓዊነትን ለማስከበር የተደነገጉ ናቸው። በተመሳሳይ መልኩም የኢፌድሪ ሕገ መንግሥትም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በመገንባት ሰብዓዊ መብቶችን ማስከበር በሚያስችል መልኩ የተቀረፀ ነው።

የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያስከብሩ ወይም መከበራቸውን የሚከታተሉ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትም በአገራችን አሉ። በዋናነትም የምርጫ ቦርድ፣ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ ተቋም፣ የፌዴራል ስነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን፣ የፍትሕ ተቋማት፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ክልላዊ ምክር ቤቶች፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት፣ እና

ዋናው ኦዲተር ቢሮ ይገኙባቸዋል። እነዚህ ተቋማት ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መጠናከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው።

የዴሞክራሲ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ ዴሞክራሲን በስራ ላይ ማዋልም ሆነ የዜጎችን ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ አይቻልም።እነዚህ ተቋማት በሌሉበት ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማስጠበቅ አይቻልም።

## 12.3 የሃይማኖት መቻቻል፣ ሰላምና ልማት

- በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት ማህበረሰብ ወይም ህብረተሰብ ውስጥ መቻቻል ለምን ይጠቅማል?

የእርስ በርስ መከባበር፣ በጋራና በሰላም ለመኖር፣ ለመማርና ለመስራት ዋና መሰረት ነው። አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ የሌሎች ተማሪዎችን መብቶች ማክበር አለበት። የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል በመሆናችሁም ታላላቆቻችሁንም ሆነ ታናናሾቻችሁን ማክበር ይጠበቅባችኋል። እያንዳንዱ ተማሪ የፈለገውን ሃይማኖት የመከተል መብት እንዳለው ሁሉ የሌሎችን መብቶች መጣስ የለበትም። ስለዚህ የግለሰቦችን የሃይማኖትና የባህል እኩልነት ማክበር ያስፈልጋል። በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት ህብረተሰብ ውስጥ የሚኖር እያንዳንዱ ሰው መረዳት ያለበት የሃይማኖት መቻቻል ለመኖር የሚያስገድዱ ሁለት ሁኔታዎች መኖራቸውን ነው። እነርሱም በሃይማኖቶች መካከል ልዩነቶች መኖራቸውንና ልዩነቶቹን በመረዳት እውቅና መስጠት የሚሉት ናቸው።

ሰዎች የፈለጉትን ሃይማኖት የመከተል መብት እንዲሁም የሌሎችን ሃይማኖት መብቶች የማክበር ኃላፊነቶች አሉባቸው። በሰላም መኖርና በሃገራዊ ልማት ውስጥ መሳተፍ ለዴሞክራሲ ስርዓት መጠናከር ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ አለው። ይህን እውን ለማድረግም በሕብረተሰቡ ውስጥ መቻቻል መኖር አለበት። በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ለሌሎች ሰዎች መብቶች ቀና የሆነ አመለካከት ሊያዳብሩ ይገባል።

በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት ህብረተሰብ ውስጥ የሃማኖት መቻቻል መኖር የሚከተሉት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፦

ሀ) ባህላዊና ማህበራዊ መስተጋብር፤ እንዲሁም አንድነት እንዲኖር፤

ለ) የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮችን ሥርዓቶችና እሴቶችን ማክበር ያበረታታል፡፡

ሐ) የአንድነት መንፈስን በማጠናከር በአካባቢና በሃገራዊ የልማት ስራዎች መሳተፍ ያስችላል፡፡

### 12.3.1 ሥነ-ምግባር በኢኮኖሚ ውስጥ

- በኢኮኖሚ ውስጥ የሥነ-ምግበር ጉዳዮች ምንን የተመለከቱ ናቸው?
- ሥነ-ምግባርን በንግድ ስራ ከተሰማሩ ሰዎች አንፃር ግለፁ፡፡

አንድን የንግድ ስራ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለማካሄድ በሕጎችና በደንቦች መመራት አለበት፡፡ በንግድና በኢኮኖሚዊ ስራዎች የተሰማሩ ሰዎች ስራዎቻቸውን ሥነ-ምግባር በተላበሰ መንገድ ከሰሩ ለህብረተሰቡ ደህንነትና ለሀገር እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ በኢኮኖሚው ዘርፍ የነጋዴዎችን፤ የተጠቃሚዎችን፤ ሕዝባዊ አመራሮችና የሌሎችን ባለድርሻ አካላትን መብቶችና ግዴታዎች የሆኑትን የሚከተሉትን ነጥቦችን ተመልከቱ፡፡

### ሀ) የነጋዴዎች መብቶችና ኃላፊነቶች

| መብቶች | ኃላፊነቶች |
|---|---|
| • ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ማግኘት፣<br>• የሕግ ከለላ ወይም ጥበቃ ማግኘት፣<br>• ንግድን በየትኛውም ያገሪቱ ክፍል ማካሄድ፣<br>• ዕቃዎችና አገልግሎቶችን መግዛትና መሸጥ፣<br>• ተገቢ ትርፍ ማግኘት፣<br>• በማህበር መደራጀት፣ | • ሥነ-ምግባር ያላቸውን የንግድ አሰራሮች መተግበር<br>- ለጠጣርና ፈሳሽ ዕቃዎች ትክክለኛ የክብደት መጠን መለኪያ መጠቀም፣<br>- ሰዎች ለከፈሉት ገንዘብ ተመጣጣኝ የሆኑ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን መሸጥ፣<br>- በደንበኛ ወይም በተጠቃሚ ላይ ምንም ዓይነት የጤና ጉድለት የሚያስከትሉ ሸቀጦችን አለመሸጥ፣ለምሳሌ፡- ምግቦች፤ መድኃኒቶች፤ ኬሚካሎች ወዘተ.<br>• ሕጋዊ ግዴታዎችን ማክበር (ለምሳሌ፡- ቀረጥ መክፈል፡ ተጨማሪ እሴት ቀረጥ መክፈል፤ በሕግ በተከለከሉ የንግድ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አለመሳተፍ፤ ለምሳሌ፡- አደንዛዥ ዕፅ ማዟዟር፤ የጦር መሳሪያ መነገድ፤ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እና የኮትሮባንድ ንግድ፤ በሕገወጥ የኢኮኖሚ ድርጊቶችን መታገልና ማጋለጥ የመሳሰሉ ናቸው፡፡<br>• የተጨማሪ እሴት ቀረጥ መሰበሰብ፣<br>• ለተጠቃሚዎች ትክክለኛ መረጃ መስጠት፣ |

## ለ) የተጠቃሚዎች መብቶችና ኃላፊነቶች

| መብቶች | ኃላፊነቶች |
| --- | --- |
| • ለከፈሉት ዋጋ የሚመጣጠን ማቴሪያሎችና አገልግሎቶችን መግዛት፣<br>- ማቴሪያሎች ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን መግዛት፤<br>- /ቴክኒካዊና ሞያዊ አገልግሎቶችን እንደማስተማር፤ ማማከርና የጥገና አገልግሎቶች/<br>• በሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት የመደራጀትን እና የሸማቾችን መብቶች ማስከበር፣<br>• በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሥነ-ምግባር ጥሰቶችና ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎች ሲኖሩ ለሚመለከተው ህጋዊ ተቋም መረጃ መስጠት ለምሳሌ፡- ቀረጥ ማጭበርበርና አደንዛዥ እፅ ዝውውር፣ የጦር መሳሪያ ዝውውር፣ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ሌሎች የንግድ እንቅስቃሴዎች፣<br>• የሕግ ጥበቃ ማግኘት፣ | • ሥነ-ምግባር የጎደላቸውን ሰዎች ተግባራት ማጋለጥ ለምሳሌ፡- ለክብደት ኪሎ፤ ለፈሳሽ ሊትር፤ ለርዝማኔ ሜትርና የማቴሪያሎችን መጠንና ጥራት ማጭበርበር፤<br>• የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፉባቸው ቁሳቁሶች፤ አላስፈላጊ ባዕድ ነገሮችን በጥራጥሬ እህሎች በጤፍና በቅቤ የሚጨምሩትን ማጋለጥ፣<br>• ተጨማሪ እሴት ቀረጥን መክፈል እንደሚገባና በዚህ ጉዳይ ላይ ከሕግ ውጪ በሚንቀሳቀሱ ላይ የማጋለጥ ስራ መስራት፤ |

## ሐ) የመንግስት ወይም የሕዝባዊ አመራሮች ሚና በኢኮኖሚ ውስጥ፤

- የነጋዴውንም ሆነ የተጠቃሚዎችን ደህንነት የመጠበቅ መብትና ኃላፊነት፣
- ሕገ ወጥ ሥነ-ምግባር የጎደላቸው እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ የማስተካከልና ንግዱን የማገድ መብት፣
- የሸማቾችና የአምራቾች ማህበራት የማቋቋም መብትና ኃላፊነት፣
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በገበያ ውስጥ ጣልቃ በመግባት መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ላይ ድጎማ በማድረግ ገብያውን ማረጋጋት ለምሳሌ፡- ስኳር፤ ዘይት፡ ማዳበሪያ፤ ሲሚንቶ፤ ወዘተ
- ፍትሐዊና ቀልጣፋ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲኖር ለማስቻል የንግድ መመሪያ ሰነዶችን በማዘጋጀት የመተባበር መብትና ኃላፊነት፣
- ሸማቾች ወይም ተጠቃሚዎችን በፍትሐዊነት መስተናገዳቸውን ማረጋገጥ፣
- በመንግስት ስራ ላይ ከሙስና ነፃ መሆን፣
- በስልጣን በመንግስት ቢሮና ሀብት አለአግባብ መጠቀምን አለመታገስ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት አካላት በጋራ በመሆን በማህበረሰብና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጠቃሚ ሚናዎችን መጫወት አለባቸው፡፡ ይህ እውን ሊሆን የሚችለው ሁሉም ያላቸውን መብቶችና ያለባቸውን ኃላፊነቶች በአግባቡ ሲጠቀሙና ሲተገብሩ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ነው ሥነ-ምግባርና ፍትሐዊነት በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊና በፖለቲካ መስኮች የሚሰፍነው፡፡

**መልመጃ 5**

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ፡፡**

1. በኢኮኖሚ ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ አካላት የሚኖራቸው ተጽእኖ ምንድን ነው?
2. በሥነ-ምግባርና በኢኮኖሚያዊ እድገት መካከል ባለው ግኑኝነት ላይ ተወያዩ፡፡

## 12.3.2 ምክንያታዊ የችግር አፈታት ለሀገር ልማት

- ምክንያታዊ ባሕሪ ምንድን ነው?
- ምክንያታዊ ባልሆነና ምክንያታዊ በሆነ ባህሪ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

የሰው ልጆች ምክንያታዊ የሆኑና የተወሰኑ የግብረገብ እሴቶችን በመከተል የራሳቸውንና የሌሎቹን ፍላጎቶች የሚያሚሉ ናቸው፡፡ ከኢኮኖሚና ከንግድ ጋር በተያያዙ ዘርፎች ውስጥ ምክንያታዊ ባሕሪ ማለት የሸማቹንና የተጠቃሚውን ፍላጎቶች በብዛትና በጥራት የሚያረኩ አገልግሎቶችንና ምርቶችን ማቅረብ ማለት ነው፡፡ አንድን ባሕሪ ምክንያታዊ ነው የሚባለው ያንን ሥራ በተመለከተ የተቀመጡትን የሥነ-ምግባር ደረጃዎችን ተከትሎ ሲሰራ ነው፡፡ አንድ ምክንያታዊ የሆነ ነጋዴ በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ ውስጥ ያሉትን ኢኮኖሚያዊና የሥነ ምግባር ጉዳዮችን ይሰራል፡፡ እንደዚህ ያለ ነጋዴ ዓላማው ከትርፍ በተጨማሪ ደንበኞቹ የሚፈልጓቸውን ነገሮች ሥነ-ምግባር በተሞላበት አሰራር በማቅረብ ተገቢ የሆነ ትርፍ ማግኘት ነው፡፡

በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ አንድ ግለሰብ የተገልጋዩን ፍላጎትና ጥቅም ቅድሚያ ሳይሰጥ በግል ጥቅም ላይ ብቻ ያተኮረ ከሆነ የንግዱን ሥነ-ምግባር በትክክል ተግብሯል ማለት አይቻልም፡፡ ይህም ማለት የሸማቹን እርካታ እውን ከማድረግ በተቃራኒ የሚፈጸም ተቀባይነት የሌለው ምግባረ ብልሹ የንግድ ክንውን ይሆናል ማለት ነው፡፡ በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ሥነ-

ምግባር ማለት ማንኛውንም የንግድ ሥራ የሸማቹን ፍላጎት በማርካት ከሥራውም ተጠቃሚ መሆን ማለት ነው፡፡

**አቶ መረሳ**

አቶ መረሳ የተያዩ ዕቃዎች የሚሸጥበት ሱቅ ባለቤት ናቸው፡፡ በሱቁ ውስጥ የተለያዩ ጥራት ያሏቸውና የጥራት ደረጃቸውም ዝቅ ያሉ ዕቃዎች ይሸጣሉ፡፡ አቶ መረሳ በርካታ ዕቃዎችን ለሚገዙ ደንበኞች ጥራት ያላቸውን ዕቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ይሸጡላቸዋል፡፡ የምግብ ዘይትና ሌሎች የጥራት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ዕቃዎችን ከመንደር ነጋዴዎች ይገዛሉ፡፡ እነዚህንም ተመሳሳይ በሆኑ ጥራት ያላቸው ዕቃዎች በታሸጉበት ማሸጊያ እያመሳሰሉ ይሸጣሉ፡፡

አቶ መረሳ ለደንበኞቹ እነዚህን ዕቃዎች ኦሪጂናል በማስመሰል ጥራት ባላቸው ምርቶች ዋጋ ይሸጡላቸዋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አቶ መረሳ ዕቃዎችን ሲሸጡ የተጨማሪ እሴት ቀረጥ አይሰበስቡም፡፡ የአቶ መረሳ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ሃዳስ ባለቤታቸው በሚሰሩት ስነ ምግባር በጎደለው ሥራ ስለማይስማሙ ለደንበኞቹ የዕቃዎቹን ትክክለኛ የጥራት ደረጃ ይነግሯቸዋል፡፡ የተጨማሪ እሴት ቀረጥም በአግባቡ ይሰበስባሉ፡፡

**መልመጃ 6**

**ከላይ የቀረበውን አስረጂ መሰረት በማድረግ በሚከተሉትን ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡**

1. ምክንያታዊና ምክንያታዊ ያልሆኑ የንግድ ባሕሪያትን በጉዳዩ ላይ በመመስረት መልሱ፡፡
2. ምክንያታዊ የችግር አፈታት በንግድ ሥራ ውስጥ እንዴት ይተገበራል፡፡

## 12.4 የሃይማኖት ብዝሃነትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ተሞክሮ

### 12.4.1 የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች ከሆኑ ግለሰቦች ወይም ሕዝቦች ጋር መኖር

በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች አብሮ መኖር የረጅም ጊዜ ልምድ ነው፡፡ በተለይም የሃይማኖት መቻቻል በሀገሪቱ ውስጥ ረዥም ታሪክ አለው፡፡ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች መንፈሳዊ እምነቶቻቸውን የሌሎችን የእምነት መብቶች በማይነካ ሁኔታ ሲተገብሩ ቆይተዋል፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ ሁሉም የሃይማኖት ተከታዮች በሰላም አብረው ኖረዋል፤ አሁንም እየኖሩ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ሁሉም ሃይማኖቶች በሕገመንግሥቱ እኩልነታቸው

ተረጋግጧል፡፡ ይህም በተግባርም እውን ሆኗል፡፡ ስለዚህ እናንተም እንደተማሪነታችሁ ሕገመንግሥቱን በማክበርና በማስከበር ለሃይማኖት መቻቻል እሴት መጎልበት ሃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በቤተሰብ ውስጥ ያለ የግብረገባዊ ሕይወት የግል ግብረገብ እሴቶች መሰረት ነው፡፡ የአንድ ግለሰብ የግብረገብ እሴቶች በቤተሰቡ አባላት የእለት ተእለት ድርጊቶች መልካም ወይም መጥፎ ተጽእኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡ በተመሳሳይም የተማሪዎች ባሕሪያት በጓደኞቻቸው ድርጊቶችና በትምህርት ቤት ሕጎችና ደንቦች  ተጽእኖ ሊያደርስ ይችላል፡፡ ከዚህም የተነሳ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና ትምህርት ቤት የተማሪዎችንና በአጠቃላይም የዜጎችን የግብረገብ እሴቶች የመቅረጽ ሚናን ይጫወታሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሕፃናትና ወጣቶች ማህበራዊ ተቀባይነት ያላቸውን የግብረገብ እሴቶች ላይ የተመሰረቱ ድርጊቶችን በመተው ሕብረተሰቡን በሚጎዱ ድርጊቶች ይሳተፋሉ፡፡ እነዚህ የወጣት የግብረገብ ጥሰት ችግሮች ተባዝተውና ተስፋፍተው የሕብረተሰቡና የሀገሪቱ ቁልፍ ችግሮች ወደ መሆን ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ኃላፊነት ያላቸው የሕብረተሰቡ አባላትና ተቋማት እንደነዚህ ያሉትን ችግሮች ለመከላከልና ለማስወገድ ስልቶችን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ የማገዙ ጉዳይ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ ይህም እውን ሊሆን የሚችለው ሥርዓቱን የሚገነቡና የሚጠብቁ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን በመገንባት ነው፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ተቋማት በኢትዮጵያ ውስጥ ተቋቁመው የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በኢኮኖሚ ውስጥ ሥነ-ምግባር የሕብረተሰቡን ሆነ የኢኮኖሚውን ደህንነት የሚያረጋግጥና የሰላም፣ የዴሞክራሲና የዘላቂ ልማት ጉዞን የሚያቃና ነው፡፡

የሃይማኖት ብዝሃነት ያላት ኢትዮጵያ ረዥም የሃይማኖት መቻቻል ታሪክ ያላት ሀገር በመሆኗ ሕብረተሰቡን ባሳተፈ መንገድ ምክንያታዊና አሳማኝ የሆኑ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አፈታት ዘዴዎች አሏት፡፡

## ቁልፍ ቃላት

**የወጣት ችግሮች፡-** በሕፃናትና በወጣቶች የሚፈጠሩ ማህበራዊ ችግሮች

**ማህበራዊ የግብረገብነት ችግሮች፡-** የግለሰብ የግብረገብ ችግሮች ወደ ቡድን ደረጃ በማደግ የሕብረተሰቡ ዋና ችግሮች ሲሆኑ

**ሥነ-ምግባር በኢኮኖሚ ውስጥ፡-** ሀቀኛና ኃላፊነትን ተከትሎ የሚከናወን የኢኮኖሚና የንግድ እንቅስቃሴ

**ምክንያታዊ ባህሪ፡-** በሥነ-ምግባር ተቀባይነት ወዳላቸው ድርጊቶች የሚመራ በግብረገብ እሴቶች ላይ የተመረኮዘ ባህሪ

**የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በደብተራች ላይ ከገለበጣችሁ በኋላ መልሱ።**

**I. የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱን በደብተራችሁ ጻፉት።**

1. የግብረገብ ችግሮች መንስኤዎች የቤተሰብ አባላት ብቻ ናቸው።
2. የሃማኖት ተቋማት በትምህርት ቤት አካባቢ የሚታዩ የግብረገብ ችግሮችን ለመከላከልና ከተከሰቱም መፍትሔ ለማፈላለግ ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ።
3. ለቤተሰብ፣ለትምህርት ቤቶችና ለሃይማኖት ተቋማት ሁሉም የግብረገብ እሴቶቻቸው የጋራ ናቸው።
4. በኢኮኖሚ ውስጥ ያሉ ሥነ-ምግባር የጎደላቸው አሰራሮች ዘላቂነት ላላው ልማት ጠቃሚ አይደሉም።

**II. በ"ሀ" ስር ያሉትን ቃላትና ሐረጎች በ"ለ" ስር ከተቀመጡት መግለጫዎች ጋር አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 1. ምክንያታዊ ባህሪ | ሀ. የሌሎችን ሃይማኖታዊ መብቶች በማክበር፣ በጋራ መስራት፣በሰላም አብሮ መኖር፣ |
| 2. የሃይማኖት መብቶችን ማክበር | ለ. ከአዋቂዎች የግብረገብነት ባህሪያት ጋር የተዛመዱ ችግሮች |
| 3.የኢኮኖሚ ወንጀል | ሐ. በግብረገባዊና እውነተኛ አሰራሮች ላይ ወደተመሰረቱ |

| | |
|---|---|
| | ድርጊቶች የሚያመሩ ባህሪያት |
| 4.የሃይማኖት መቻቻል | መ. በሕፃናትና ወጣቶች የሚፈጸሙ የግብረገብ ጥሰት ድርጊቶች |
| | ሠ. በመገበያየት ወቅት የሚፈጸሙ ሕገወጥ የሆኑ መለኪያዎችን መጠቀም |
| | ረ. የዴሞክራሲ አሰራርን ከሚያጎናጽፉ ጉዳዮች አንዱ |
| | ሰ. ባእድ ነገሮችን በምርት ውስጥ በመጨመር መሸጥ |

**III. ጥያቄዎቹን በደብተራችሁ ላይ ከገለበጣችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ በተሰጠው ቦታ ላይ ሙሉ።**

1. አንድ ሰው ለሌሎች ሃይማኖቶች ያላው ክብር፤ የሃይማኖት ነክ ችግሮችን መፍታትና አብሮ በመኖር በልማት በጋራ መሳተፍ ____________________ ይባላል።
2. ለተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች አብረው ጎን ለጎን ወይም ተደባልቀው መኖር ____________________ይባላል።
3. በሰዎች አስተሳሰብ ውስጥ ያሉና በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ድርጊት ለማከናወን □ሚረ□ ______________ ይባላሉ።

**IV. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።**

1. የሃይማኖት ብዝሃነት ማለት
   - ሀ) በማህበረሰቡ ውስጥ ከአንድ በላይ ሃማኖት መኖር
   - ለ) በርካታ የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች በጋራ መኖር
   - ሐ) ማህበረሰቡ ስለሃይማኖት ያለው ግንዛቤ
   - መ) የበርካታ ሃይማኖቶች ተከታዮች በሰላም አብሮ መኖርና የማህበረሰቡ አባላት ያሏቸው ቀና አመለካከት
2. ማህበራዊ የግብረገብ ጥሰት ችግር ማለት
   - ሀ) በህብረተሰቡ ውስጥ በቡድን የተፈጸሙ ግብረገብነት የጎደላቸው ድርጊቶች
   - ለ) በህብረተሰቡ ውስጥ በአንድ ወጣት የተፈጸሙ ግብረገብነት የጎደላቸው ድርጊቶች
   - ሐ) በህብረተሰቡ ውስጥ የአንድ ግለሰብ ግብረገብነት የጎደላቸው ድርጊቶች

መ) በህብረተሰቡ ውስጥ የአንድ አባል ግብረገብነት የጎደላቸው ድርጊቶች

3. የግል የግብረገብ ጥሰት ችግር ማለት

   ሀ) በህብረተሰቡ ውስጥ የአንድ ግለሰብ ግብረገብነት የጎደላቸው ድርጊቶች

   ለ) ግብረገብነት የጎደላቸው ተግባራት በህብረተሰብ ውስጥ ባሉ ቡድኖች ሲፈጸሙ

   ሐ) በህብረሰቡ አባላት ግብረገብነት የጎደለው ድርጊቶች ሲፈጸሙ

   መ) በህብረተሰቡ ውስጥ ወጣቶች የሚፈጽሟቸው የግብረገብ ጥሰት ድርጊቶች

4. በህብረተሰባችን ውስጥ በቤተሰብ፤ በትምህርት ቤትና በሃይማኖት የጋራ ተቀባይነት ያላቸው ምን በመባል ይታወቃሉ፡፡

   ሀ) የሃይማኖት ድርጊቶች

   ሐ) የግብረግብነት እሴቶች

   ለ) የግብረገብነት እሴቶች የጎደላቸው ድርጊቶች

   መ) መልሱ የለም፡፡

5. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሁኔታ በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት ህብረተሰብ ውስጥ መኖር የሌለበት ነው፡፡

   ሀ) የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችን  መብት ማክበር

   ለ) የሃይማኖት ችግሮችን ለመፍታት በጋራና በምክንያታዊነት መሳተፍ

   ሐ) ወደ ሰላማዊ አብሮ የመኖር ሁኔታ የሚያመሩ የሞራል እሴቶችን ማስተማር

   መ) በዜጎች የሃይማኖት መብቶች ላይ ልዩነት መፍጠር

## V. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡

1. በአካባቢያችሁ ካሉ ሥነ-ምግባር የጎደላቸው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች አንዱን በመምረጥ ይህ ችግር እንዴት በምክንያታዊነት ሊፈታ እንደሚችል አብራሩ፡፡
2. የወጣቶች ችግሮችን ለመፍታት ቤተሰብ፤ ትምህርት ቤትና ተቋማት የሚጫወቷቸውን ሚናዎች ዘርዝሩ፡፡
3. በኢትዮጵያ ያለውን የሃይማኖት መቻቻል ልምድ በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበት ህብረተሰብ ውስጥ ካለው የዴሞክራሲ ትግበራ ጋር በማዛመድ አብራሩ፡፡